# አማራ ስማ እራስን መከላከል የተፈጥሮ ዑደት ነው።

በሚገርም ሁኔታ የሩስያ ኦርቶዶክስ ክርስትያን እምነት ብሎም የተቀሩት የክርስቲያን ተቃዋሚዎች/ Protestant እምነቶች እስላማዊ እምነቶች፣ ህብሩ እምነቶች በብዛት ያለባቸው ሀገራት ይህንን የተፈጥሮ መብት ጠንቅቀው ያውቃሉ/ ይተገብሩትማል። ድሮ አያቶቻችን ይህ ጉዳይ አያሳስባቸውም ነበር።

ምክንያቱም፣ ነጋስታታቹ ሳይቆርቡ፣ ሳይናዘዙ፣ የግብር ገብ ትምህርቶችን ሳይቀምሱ በፊት፣ መንበር እና ስልጣን አይጨብጡም ነበር። የዛሬው ግን የተገላቢጦች ሆኗል፣ ከቤተ ክህነት፣ እስከ ቤት መንግስት፣ እስከ ፍትህ ምክር ቤት ሁሉም ነገር ብላሽ፣ ንዝር ሆኗል፣ ካህኑም፣ ፓስተሩም፣ ሼኩም ነጋዴ ሆነዋል። በተጨማሪም ከመንግስት ነኝ ብለው ከተቀመጡ አምባገነኖች ጋር በጥምረት ሆነው ከእነዚህ በንዝረት ከበከኑ የእምነት ተቋማት ጋር የጦፈ ንግዳቸውን ተያይዘውታል።

ምልምል መሆናቸው የሚያሳብቀው ድርጊታቸው ደግሞ፣ ህዝበ ምእመናን የሚኖረው ለሚቀጥለው ህይወቱ ነው በሚል ህሳቤ ፣ መንግስታትን አትጣላ ሰላም ይምጣ ዘንድ እንፀልይ ህዝቡን ሌት ተቀን ያደነዝዛሉ በሰበካ። በድህነት መኖር ፅድቅና እንዴት ሊሆን ይችላል? የበረከት ህይወት እና ጤናማ የተትረፈረፈ ምርት፣ ሰላም እና ፍትህ ያለባት ሀገር፣ የላቀ አእምሮ ያለው ህይወትን እየኖሩም እኮ ፃድቅ መሆን ይቻላል። የግድ የድህነት ኑሮ መኖር እለበት እንዴ አንድ ሰው ህይማኖተኛ ወይም ፃድቅ ለመሆን። የተፈጥሮንስ መብት መጠይቅ እንዴት ሀጥያት ሊሆን ይችላል።

የአንድ ሀገር ተወላጅ ዘጋ ሆኜ፣ በሀገሬ ላይ ደረቴን ለጥጬ በነፃናት፣ ምንም ሳልሸማቀቅ የፈለኩት ቦታ መዘዋወር ሀጥያት ነው? በገዛ ሀገሬ ላይ የሚካሔዱትን መልካሙንም ጎጂዎችን መቃወም ወይም መደገፍ ሃጥያት ነው ወይ? አንዳንዴ እንስሳት ከሰው እጅግ በነፃነት የሚኖሩ ፍጥሮች ናቸው ብዬ አስባለሁ።

እንስሳት እርሳቸውን ለመከላከል የማንንም ባለ ስልጣን ፈቃድ አይጠይቁም፣ ሲፈጠሩ በውስጣቸው ያለ እራስ ተዛዥ ባህርያቸው ቀድሞ የዳበረ ነው። ግን እኛ ሰዎች ምን ነካን ይችን ነገር እንኳን ለማጤን?

ሔኖክ ተሾመ